## መልመጃ አንድ÷ ተዋንያን
**Exercise One: Actors**

1. ይህ ኪነት የተከናወነው የት ነው?
2. የአቶ ዋሴ ልጆች ስንት ናቸው?
3. የከበደ አባት ማን ይባላሉ?
4. በዚህ ኪነት ውስጥ ስንት ተዋንያን ተሳትፈዋል?
5. የአሳት የሥራ ድርሻ ምንድን ነው?
6. ከበደ ለምን ሽልማት ፈለገ?
7. የክፍል ኃላፊዎች ሚና/የሥራ ድርሻ ምንድን ነው?
8. ልጁ በትምህርት ውጤቱ ቤተ ሰቦቹ ተደስተዋል?
9. የልጁ ፍላጎትና ምኞት ምን እንደሚመስል ግለጹ?
10. አሳት በወንድሙ ልጅ የተደሰተ ይመስላል?

## መልመጃ ሁለት÷ምንባብ ÷ትክክለኛውን መልሰ ከ ሀ÷ ለ እና ሐ ምረጡ
**Exercise Two: Reading Comprehension. Choose the right answer between A, B, and C.**

1. አልጠራጠርም ማለት

ሀ. አልታመንም

ለ. በውጤቴ ትደሰታለህ

ሐ. ዉጤቴ አያስደስትም

2. እልል በቅምጤ

ሀ. መደሰት ተቀምጦ ነው

ለ. መደሰት ቆሞ ብቻ ነው

ሐ. ከፍተኛ ደስታ ማግኘት

3. ምን ይፈይዳል?

ሀ. ምን ያደርጋል?

ለ. መቼ ይመጣል?

ሐ. መልሱ አልተጠቀመም

4. <u>እንካ የምስክር ወረቀቴን!</u> አንደኛ ነው የወጣሁት። ወረቀቱን ከሰጠው ለምን አንደኛ መውጣቱን ተናገረ?

ሀ. አባቱን ስለሚፈራ

ለ. አባቱ ማንበብ እንደ ማይችል ሰለሚያውቅ

ሐ. አንደኛ መውጣቱን ሁሉንም ሰለሚያስደስት አባቱን ለማታለል ነው

5. ምን አግኝታችሁ ነው የምትሳሳሙት?

ሀ. ያስደሰታችሁ አዲስ ነገር አለ?

ለ. የሚያረካችሁ ነገር፥ደስታ የሚፈጥር ነገር ተከስቷል

ሐ. ሁለቱም ትክክል ናቸው

6. ብትወልድም፥ ብትከብድም ላንተ ትሁን

ሀ. ላሚ የምታስገኘው ጥቅም በከፊል ላንተ ይሁን

ለ. ግማሹ ላንተ ይሁን

ሐ. ሁሉም ላንተ ይሁን

7. ጥጃ ማለት

ሀ. የላም ልጅ

ለ. የላም አባት

ሐ. የላም ሽንት

8. <u>ይልቁንም</u> ማለት

ሀ. ይህም ቀርቶ

ለ. ከዚህ ይልቅ

ሐ. ሁሉም

9. የኔ <u>ሺ_መክት</u> ና ሳመኝ መባሉ ምንን ያመለክታል?

ሀ. ቅያሜን

ለ. ደስታን

ሐ. እፍረትን

10. በምንባቡ መሰረት ልጅን___________ያጠቃዋል።

ሀ. ተጠራጣሪነት

ለ. ብስለት

ሐ. ብልጠት

## መልመጃ ሦስት፥ በክፍል ሀ ያሉትን ቃላት ወይም አባባሎች ከክፍል ለ ጋር አዛምዱ

**Exercise Three: Match these words or expressions in column A with their equivalent in column B.**

| አምድ ሀ<br>**Column A** | አምድ ለ<br>**Column B** |
|---|---|
| 1. የልጅ ነገር ቦታውን አይረሳ | ሀ. ያንተ ድርሻ |
| 2. ሀብት የመያዝ እርሾ | ለ. አዋቂ፥ ምሁር |
| 3. አንተ በርታና እለፍ እንጂ | ሐ. አንተ ጠንክረህ አጥና |
| 4. በዱቤ | መ. አዎንታዊ ተቀባይነት |
| 5. አጎት | ሠ. ሺህ አውል |
| 6. እሺ | ረ. የንብረት ማፍራት መጀመሪያ |
| 7. እግዜር ይባርክህ ልጄ | ሰ. ቆይቶ የሚከፈል ዕዳ |
| 8. አንዱ በቃኝ | ሸ. ያባት ወይም የናት ወንድም |
| 9. ሊቅ ሆነልን | ቀ. የብስለት እጥረትን የሚያመለክት |
| 10. ጉልማህ | በ. ምርቃት |

## መልመጃ አራት፥ በመዝገበ ቃላት ውስጥ ያሉትን ቃላት በመጠቀም ክፍት ቦታዎችን ሙሉ

**Exercise Four: Fill in the blanks by using words from the glossary**

1. ለበጎ ሥራ ወይም ብልጫ ተግባር የሚሰጥ____________
2. ከሁሉ የበለጠ ነጥብ አገኘ____________
3. በፍጥነት/በቅልጥፍና ደረሰ ____________
4. በሬ ደረጃ ያልደረሰ ቆይቶ በሬ የሚሆን____________
5. እኔን የሚያስደስተኝ____________
6. ቆይታ ላም የምትሆን እንስሳ____________
7. ከመጠን በላይ መደሰት____________
8. ከመጀመሪያ ልጅ ቀጥሎ የሚወለድ ልጅ____________
9. የልጅ ነገር ብስለት ይኖረዋል ለማለት የተባለ ያድናቆት ሐረግ____________
10. ስትሰቃይ ትኖራለህ____________

## መልመጃ አምስት፥ የተሰመሩትን ቃላት በተመለከተ ጥያቄዎች ጠይቁ

**Exercise Five: Ask questions corresponding to the underlined words**

1. ቁራሽ
2. በዱቤ
3. ያሳስማችኋል
4. ይልቁንም
5. ብቻውን
6. ምን ያደርጉልኛል
7. እየበላ ያለቅሳል
8. አዲስ አበባን ትንፈላሰስባታለህ
9. አጠራቅሞ
10. ትንሽ በትንሽ

## መልመጃ ስድስት፥የማዳመጥ ምንባብ፥ ውይይቱን ተመልከቱና በእያንዳንዱ መሥመር ላይ ያላችሁን አስተያየት ስጡ።

**Exercise Six: Listening comprehension. Watch the conversation and comment each line**

ልጅ - ምን ያደርግልኛል ሀብት?

አጎት - እውነትም የልጅ ነገር! ከበርቴ፥ ባለፀጋ፥ ሀብታም የሚኮነው እኮ ሀብት በትንሽ በትንሹ አጠራቅሞ ነው እንጂ/እኮ፤ አለበለዚያ ድሃ ሆነህ ስታክ ትኖራለህ! የትምህርትም አንዱ ጥቅም ይህ ነው እኮ! የተሻለ ኑሮ ለመኖር።

ልጅ - ታዲያ አዲሰ አበባን ሳላይ ልቀር ነው?

አጎት - ከሁለት ዓመት በኋላ ስምንተኛ ክፍል ስትጨርስ/ስታልፍ ወደ ዘጠነኛ ክፍል ስትዛወር ማለት ነው የግድ አዲስ አበባ ትሄድ የለ?! አንተ በርታና እለፍ እንጂ አዲሰ አበባን ትንፈላሰስባታለህ!

ልጅ - አሁን ገና ገባኝ! እሺ! እሺ! አጎቴ! መቶ በመቶ ባላመጣ ደግሞ እኔ አይደለሁም!

አጎት - መቶ ደግሞ ምንድን ነው?

ልጅ - ፈተናዋን ድፍን አድርጎ ማግኘት ነዋ!

አጎት - ሙሉውን ማለት ነው?

አጎት - መቼም ልጅ የብልጠቱን ያህል ብስለት የለውም፥ካሁኑ የግል ሀብት ማፍራት ማለት እኮ ሀብት የማካበት/የመያዝ እርሾ ነው።

አባት - ልጄ አንደኛ ወጣ እኮ! ሊቅ ሆነልን።

አጎት - ይሄ ነው! አንዱ በቃኝ! የኔ ሺህ መክት! ና ሳመኝ!

ልጅ - መጀመሪያ ያልኩህን ፈጽምልኝ እንጂ

አባት - በዱቤ ነው እንዴ

አባት - አልፈልግም ጊደር አጎቴ ወይፈን...

አጎት - ይሄ ነው አንዱ በቃኝ የኔ ሺመክት ና ሳመኝ

ልጅ - ሁለታችሁም ሽጣችሁ አዲስ አበባን አሳዩኝ

ልጅ - አጎቴ አንተስ ምን ትሸልመኛለህ?

## <u>መልመጃ ሰባት፥ አዎንታ ወይም አሉታ ጥያቄዎች</u>

**Exercise Seven: yes or no questions**

| | አዎን | አይደለም |
|---|---|---|
| 1. ከበደ ሰነፍ ተማሪ ነው። | | |
| 2. የከበደ አባት ዳኛ ናቸው። | | |
| 3. የትምህርት መረጃ የተማሪ ጠቅላላ ውጤትን ያሳያል። | | |
| 4. ከበደ የሁለተኛ ክፍል ተማሪ ነው። | | |
| 5. የትምህርት ቤት መጨረሻ ሰኔ ሰላሳ ነው። | | |
| 6. አባት ለልጁ የመቶ ብር ሽልማት ሰጠው። | | |
| 7. ሀብታም ማለት ባለ ፀጋ ማለት ነው። | | |
| 8. የትምህርት ውጤቱ ያላመረ ተማሪ ደካማ/ሰነፍ ይባላል። | | |
| 9. እግዜር ይባርክህ ማለት ምርቃት ነው። | | |
| 10. ከበደ አዲስ አበባ ለመሄድ ፍላጎትና ምኞት አለው። | | |

## <u>መልመጃ ስምንት፥ ተቃራኒ የሆኑትን ቃላት በመልመጃው ውስጥ ፈልጉ</u>

**Exercise Eight: Find the antonyms of these words in the text.**

1. ጎበዝ
2. ድሃ
3. መሳቅ
4. ደካማ ኑሮ
5. ውጪ
6. መረገም
7. አለመፈለግ
8. አለመመኘት
9. ጎዶሎ
10. አስቀያሚ/መጥፎ/ብልሹ

## <u>መልመጃ ዘጠኝ፥ ውይይቱን በራሳችሁ አባባል/ቃላት አሳጥራችሁ ጻፉ</u>

**Exercise Nine: Summarize the dialogue in your own words.**

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

## <u>መልመጃ አስር፥ ኪነት መሥራት። ኪነቱን ተለማምዳችሁ የከተማውን አማርኛ በመጠቀም ዝግጅት አቅርቡ። ይህ ዝግጅት ባህሉን፥ አቀራረቡን እና ሌሎች የቋንቋው ስልቶች እንዲገቡ ያስፈልጋል።</u>

**Exercise Ten: Role play:** Rehearse and perform the skit by using urban Amharic. Be mindful to reflect the local culture, gestures and other kinesics aspects of language